# የወያኔ ባንዳዎች በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በአመራር ውስጥ ሰርገው ገብተዋል

ከባይሳ ተክሉ

በህዳር ወር መጨረሻ በዚህ 2006 ዓመት በአትላንታ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ የእድር ስብሰባ በዛሬው ቀን 3 ፒም(እአአ) ላይ አለ ተብሎ ቤተ ክርስቲያን ሲነገር ሰምቼ በመሄድ ያየሁትን፣የሰማሁትንና የታዘብኩትን በዚች አጭር ማስታወሻ ለማካፈል ነው።

ስብሰባው ከተባለው ስዓት አንድ ስአት ተኩል ዘግይቶ የተጀመረ ሲሆን ከ450 አባላት በላይ አለው የተባለለት 60 ሰዎች የሚሆኑ ብቻ ነበር የተገኘው።የስብሰባው መሪ የሆኑት ወ/ሮ ከዚህ የበለጥ ብንጠብቅ ብዙ ሰው አይመጣም በማለት አሁንም ጊዜ ለማራዘም በማሰብ ይመስላል ሁለት ስዓት ያህል ቀድመን ለተገኘነው ይቅርታም፣ምስጋናም ሳይወጣት 4:45 ፒም ላይ ተጀመረ። በመድረኩም ላይ ስድስት የሚሆኑ ኮሚቴ አባላትን አስተዋወቀች።በመቀጠልም የሁለት የሥራ ሪፖርቶች በየተራ በ15 ና በ20 ደቂቃ ውስጥ ተሰማና እረፍት ስትል ስብሰባውን ለመበተን መሪ አወጀች።

የእረፍቱም ጊዜ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ቡና፣ ለስላሳና ዳቦ ለመሸጥ ያቀረበች አለችና እየገዛችሁ ተዝናኑ ተብሎ ተነገረ። ግለሰቧም እንደታቀደላት ገበያዋን አጧጧፈች። ወደ 15 ደቂቃ በዚህ የገባያ ዝውውር አለቀ። የኮሚኒቲው የሰብሰባ አዳራሽና ጊዜ ለግለሰቦች ሸርክናና የወዳጅነት ትብብርና ጥቅም እንደዋለ ትዝብት አንድ አልኩኝ።

ስብሰባው ከእረፍት መልስ ተጀመረና ቀሪዎቹ አራት የሚሆኑ የአመራር አባላት በተከታታይ አጭርና ረዥም ሪፖርቶችን አሰሙ። ረዥሙን ሪፖት ያቀረቡት የእድሩ ሊቀመንበር በአምባሳደር የሚጠሯቸው (ማዕረግ ወይ ስም አልገባኝም) ሲሆኑ ብዙ አወዛጋቢና ሕጋዊ ጥያቄን የሚያመላክቱ አሳቦችን እንደያዙ ተገንዘብሁ።ሪፖርቱ አመታዊ ነው ድርጅቱም ከተመሰረተ አንድ አመቱ ነው።በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደ መቶ ሺህ የተጠጋ ገንዘብ እንደላቸውና ከዚህም ወጭ በማድረግ ፖስተሮችን፣በራሪ ወረቀቶችን አሳትመናል፣ የፎቶ ማንሻ ካሜራ ገዝተን ለአባላት መታወቂ $10:00 ዶላር (ብር)እያስከፈልን እንሰጣለን፣ ገቢአችን ይህን መስላል ይላል በሪፖርቱ።ጭብባው ሞቅ ያለ ነበር ። ትዝብት ሁለት ።

ከዚህም በማከታተል እስከ አሁን ለሞት እንዳልተከፈለ በመግለጽ፣ ግን አንድት አባል የእድር እርዳታ ጠይቃ ሕጉን ስለአላሟላች እንዳልተፈቀደላት አሰረድተዋል ፣ ከግለሰቧ በኩል በምን ሁኔታ ጉዳዩ ተቀባይነት እንዳገኘና እንዳላገኘ የተብራራ አልነበረም።ገቢው እያደገ ወጭ የሌለበት ነው ተባለና በዚሁ ሪፖርት ውስጥ ይህ እድር የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ጥገኛ ነው። በዚህ ምክንያትም የኮሚኒቲውን ቤት፣ መብራት፣ውሃና ሌላም በመጠቀም ብዙ ወጭዎችን ሸፍኖልናል ይላል።ቀጥሎም የእድሩ አባል ለመሆን የኮሚኒቲው አባል መሆን ግደታ ነው በማለት በጥብቅ ያሳስባል።እንድሁም ከእንግዲህ "የኢትዮጵያ ኮሚኒት ማህበር ለአስከሬን እርዳታ ማሰባሰብ ማቆሙን አውቀው ዛሬውኑ የኢ ሚ_ ማ እድር አባል

ይሁኑ" መፈክራቸው ሆኖ ሁሉም ያስተጋቡት ነበር።ትዝብት ሶስት። በአመት ውስጥ ብዙ ሰዎች ሞተዋል፣ ለ 3_ና 4ቱ ለቀብር ሥርዓት አባላቶቻቸውን ሲጠይቁ የተሰማው አምሳ ሎሚ የተባለው እድር ብቻ ነው።

ሌሎችም በመቀጠል ሂሳብና ኦዲት ፣ ሕግን በማሻሻልና በመለወጥ ላይ የተመለከቱ ሪፖርቶችን አቅርበዋል። ከዚህ ኃላ የጥያቄና መልስ ጊዜ እንደሚኖር መሪዋ ተናገረች። ለሁለት ጠያቂዎች ብቻ እፈቅዳለሁ ሲሉ 5ና 6 ሰዎች በላይ የቀረበ ሪፖርት የህዝብ የመጠየቅና የመረዳት መብት ለመግታት ብዙ ጥያቄዎች እንዳይነሱ የማድረግ ስልቷን አስቀድማ አልቀበልም ስትል አሰጠነቀቀች።ትዝብት አራት፡

ሁለት ጠያቂዎች በየተራ ተነስተው በአብዛኛው የኮሚቴ አባላትን የሚያደንቁና የሚያኩራሩ የምስጋናና የማሞካሸት አስተያት ወይ ጥያቄ አይሉት እየሰጡና እየተጨበጨበላቸው ተቀመጡ። ለተሰጠውም አስተያየት መድረኩ ላይ በሃላፊነት የተቀመጡት ሰባቱም ማን ከማን አንሽ አይነት የየስሜታቸው አሳብ በአጠፌታው አቀረቡ ። ሆኖም የሰጡት አሳብና እቅድ ሌላ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያስከትል ሆነና የጠያቂዎች እጅ ብዙ ሆኖ ይታይ ነበር።

ከብዙ መጨነቅ ጋር ለአንድ ግለሰብ ተፈቀደና አጋፋሪው የድምጽ ማጉሊያውን ሰጣው።ጠያቂውም ያቀረባችሁት ሪፖርት እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን የሰጣችሁት አስተያየት ብዙ ጥያቄዎችን አሳድሮብኛል። ይህውም ፣ እንዴት አንድ ኢትዮጵያዊ የኮሚኒቲ አባል ካልሆንክ የእድር አባል አትሆንም ይባላል? በየትኛው ሕግ ነው ? ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዚህ እድር ውስጥ የመግባት መብት አለ ። የዚህ የዚያ አባል መሆን አለብህ ተብሎ አይነፈግም ። ሕግም የለም፡ የሁላችን ችግር ነው ብለው በመጠየቅ ላይ በአለበት ወቅት፣ ከላይ ከታች እው ! ው ! ው! እያሉ በግለሰቡ ላይ በመጮኽ የጀሪ ስፐሪንገርን ሾው በማስመሰል ጠያቂውን በማዋከብ አጋፋሪዎቹ የድምጽ ማጉሊያውን እንዲነጥቁ የስብሰባው መሪዋ ከመቀመጫዋ በመወራጨት ቁጭ ብድግ እያለች ትዕዛዝ ሰጠች።አጋፋሪዎችም ማይክሮፎኑን ለመውሰድና ጠያቂውን ለማስቀመጥ ከዚያ ከዚህ ተወራጩ ግለሰቡም ጥያቄ መጠየቅ መብት አለኝ አልጨረስኩም በማለት ወደ ተሰብሳቢውም ወደ አለቆቹም እየተዟዟረ ቢመለከትም ው! ው ! ው ! ከሚለው በስተቀር የመናገር መብትን ለማስከበር ይጨርስ ብሎ የተናገረ እኔን ጨምሮ አላየሁም።አጋፋሪዎችም ግብግብ ያዙ፣ ከበባውም በዛ ሌላም ሰው ከመድረክ እየተንደረደረ በመውረድ ለማስቀመጥ፣ አልፈው ተርፈውም እንደ ፖለቲካ ድርጅት ቦታህ አይደለም ይመስላል ከስብሰባው ውጣ አሉት። ሰውየው ግን ፖሊስ ጥሩ ብሏቸው ተቀመጠ።በተሰጠው ጊዜ የፈለገውን ቢጠይቅ ምን ችግር ይሆናል? መልስ አለመስጠት የነሱም መብት ነው።ትዝብት አምስት

እኔም በቤቱ በተነሳው ጥያቄ ቢኖረኝም በሰውዬው የደረሰውን ተገንዝቤ በፍርሃት ተውጬ ዝም አልኩ። ፈሪ ለእናቱ ይቆይላት ሆነና ግልምጫ፣ ቁጣና ስድብ አይንም ላለመግብት አስቤ ጸጥ ብየ ቀረሁ።በዚህ ወቅት ብዙ ሰውች እየወጡ ሄዱ ነበር።እኔም ብዙ አቅማምቼ እስከ መጨረሻው ቆየሁ።ይህ መጥፎ፣ የፍራትና ምቸገረኝ ባህል ብናቆምና ለእውነት ብንደፋፈር ጥሩ ነው።ሌላው ትዝብት ስድስት

ትንሽ መረጋጋት ሆነና የተፈቀደላቸው ሰዎች በየተራ እተነሱ የጊዜ ገደብ ሳይገታቸው ኮሚቴዎቹን ሲያሞግሱና ሲያወድሱ ጥያቄ ይሁን አስተያየት ያለየለት ብዙ ሚያወሩና አንዱን ነገር ደጋግመውም ደጋገመውም ለማውራት ተፈቀደላቸው።አንዱም ተነስቶ ተማርን እያሉ እንደዚህ ቻይልድሽ የሆነ አሳባ ያቀርባሉ እያለ ቀደም ሲል ጥያቄ ያነሳውን የሱን ዲንቁርና የተማሩትን በማንጓጠጥ ሊያካክስ ሲሞክርና በብልግና ስውን ሲዳፈር፣ ሲዘልፍና ሲያወራ ማንም ሥነ_ሥርዓት ብሎ ለማስቆም የሞከረ አልነበረም።

የስብሰባው መሪ ወ/ሮማ ደስታዋ እንደሆነ እንጂ ሥርዓቱ_ ምግባሩም ከየት ታምጣ፣ያላት አይመስለኝም። ትዝብት ሰባት በሉ

ስብሰባው በመቀጠል የመተዳደሪያ ሕጉን ለማሻሻል፣ለማረምና ለውጥ ለማድረግ ተብሎ በአጀንዳ የተያዙትን አንቀጾች አንዱ አቀረበ። እንደሁም ሕጉን አጀንዳ አርጐ ለመነጋገር የኮሚኒቲውና የእድሩ አባላት ሁለት ሦሥተኛው(2/3)መገኘት አለበት ተባለ። በዚህ ያለው ግን እጅግ ትንሽና የእድር አባላት የተባሉ ብቻ ነበሩ። ይህ መሆኑ እየታወቀ ቀድሞም አባላት ሳይደርሰው እንደት የተለያዩ አንቀጾችን ለውይት አቀረቡ? ከዚህም በመቀጠል የአባላት መመዝገቢያና የወር ክፍያ ወደፊት ስለሚጨምር ውዝፍ ያለባችሁ እንዲሁም ለአዲስ አባልነት የምትመዘገቡ በዛሬው ቀን የስድስት ወሩን እየከፈላች ተመዝገቡ ተባለ።ለምን ይጨምራል? ምን ስለሆነና? የሚሉም ጥያቄዎሽ ተነሱ ክርክርም ተጀመረ።በአለበት ይቆይና መጨመር አለበት የጦፈ ክርክር ሆኖ ይጨመር ሁሉም ስለሚሰራ መክፈል ይችላሉ የሚሉም ተሰምተዋል።ይህ እድር ግን ለማንም ሞት ወጪ ያላደረገና እዳ የሌለበት ነው።ለምን ክፍያ እንድጨምር ታቀደ?

ስብሰባው ወደ ማጠናቀቂያው ደረሰና አንድ መንፈሳዊ አባት ፈቃድ ጠይቀው በሰላም አስጀምሮ በሰላም ለአስጨረሰን የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን፣ሞትን ይያዝልን፣ ይጠብቀን በማለትና በአባታችን ሆይ ጸሎት እንድንለያይ አድርገው ስብሰባው ተበትኗል።

በዚህ ስብሰባ ተገኝቸ ይህ የአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ያለበትን ችግር በማየቴና በመስማቴ እጅግ አሳስቦኛል፣ አዝኛለሁ። ከአሁን በፊት በአሻጥረኞች፣ ወያኔዎች እጅ ወድቆ ሲበዘበዝና አባላትም እስከማጣት ደርሶ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ደርሰው በአለፉት አራት ዓመት እጅግ እያደገ መጥቶ ከኪራይ ቤት ትንሽም ብትሆን ቤት ለመግዛትና ተጠቃሚም አባላት እየጨመረ ነበር።አሁን ግን እንዳየሁትና እንደተረዳሁት ማህበረሰቡን ያካተተና ያቀፈ ሳይሆን የግለሰቦችና የቡድን አሻጥረኞች ለራሳቸውና ስውር አላማ የሚጠቀሙት ሆኖ ያገኘሁት። በቡድን የሚጮኹ፣እነሱ ከሚፈልጉት ውጭ የማንን ጥሩ አሳብ ቢሆንም  እንኳን ተቀብሎ ማስተናገድ የማይፈልጉ ወያኔዊ የውሸትና ተንኰል መቅስፍት የተጠናወታቸው ናቸው።እነዚህ መሰሪዎች አንዳንድ ተላላና እንደመሩሽን በመሀላቸው በአመራር ላይ አስቀምጠው የኢ ሚ ማህበሩን እያመሱና እየተጠቀሙበት።

ከዚህ ስብሰባ በኃላ እንደሰማሁት አንዳንድ ጹሁፎችን እንደ አነበብኩት ደግሞ የማህበሩ ኮሚቴ አባላት ያለ አግባብ ከሕገ ሥርዓቱ ውጭ እንደተመራረጡ ነው።አስመራጭ ኮሚቴው አባላት አስመራጭም ተመራጭም በመሆን የማህበሩ የኮሚቴ አባልና የሥራ አስፈጻሚ በመሆን እየሰሩና ይህ ሲታወቅባቸው አባላትን በማበጥ ላይ ይገኛሉ።

ይህን የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የስውር አጀንዳ ያላቸው የወያኔ ንክኪነትን የተላበሱ ለራስ ጥቅምና አገልግሎት አቅደው ያሉና እንዲሁም የተለያየ የፖለቲካ ድርጅትና የቡድን፣ ራስ ወዳዶች ሰርገው በመግባት ይዘውታል።በኢትዮጵያ፣ በሕዝቧና በሰንደቅ ዓላማዋ ተቆርቋሪ እየመሰሉ ስውር ወያኔዎችና የኢትዮጵያ ጠላቶች በዚህ በውጭ አገር ሳይቀር በመሃላችን ገብተው እየከፋፈሉና እየተጠቀሙብ ነው። ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን ልጥቀስ ለኢትዮጵያ ርዳታ እየተባለ፣ ለተፈናቀሉ ሰዎች ገንዘብ በማሰባሰብ የተሰማሩ፣ተስፋ ለኢትዮጵያ እያሉ የመኖሬያቸው ገቢ ያደረጉ፣በየምክንያቱ ገንዘብ ሰብሳቢወችና ታክስ

ፎርስ ለተጐዱ ወገኖች፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በመሸጥ የሚጠቀሙና ገቢ ምንጭ ያደረጉ እንጂ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ወደው አይደለም። ይህን ለእውነት የቆመ ሁሉ ይወቅ ይረዳው።

ሌላው ደግሞ ወያኔ በአገር ቤት ብቻ አይደለም ሸርና ተንኮሉን ያሰማራው። ባንዳ ግልገሎቹን በስደት መልክና ለልዩ ሥራ ጉዳይ እያለ ያሰማራቸው ስውር ተኩላዎች በመሃላችን ሞልተዋል። የተላኩበትን እየተገበሩ እንደሆነ በዚህ በአትላንታ የኢት/ኮሚኒቲ ሕገ_ወጥ ሥራቸው ለመረዳት ተችሏል።  የዚህ ድርጅት አባል ካልሆንክ ለዚህኛው ብቁ አትሆንም የሚል ሕግ በዚህ በአሜሪካ ውስጥ የለም።የወያኔ ነው።ከየት የመጣ ነው ይህ የማስገደድ ባህሪ የወያኔ አጭበርባሪ የዘረፋ አጉል ብልጣብልጥነት ተንኮል ካልሆነ? የስድስት ወር ቀድማችሁ ክፈሉና አገልግሎቱ ከስድስት ወር በኃላ ይጀምራል ምን የሚባላል ነው? ይህ የእድር ስም ሊሰጠው የሚገባ አይመስለኝም። ለኮሚቴ አባልና አመራርም የውስጥ ደንብና የምንኖርበትም አገር ሕግና ደንብ መከተል ይኖርበታል።ይህን መራጩ ሕዝብ ማወቅ አለበት።ኮሚቴዎቹ እንደትና በማን ማን እንዴት መረጣቸው? ማን ለምን ጉዳይ ሃላፊ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።ዝምታ አስፈላጊ አይደለም።ጥያቄን ለመጠየቅና ለመረዳት ምቾትና ድፍረት ይጐለናል።በዚህም ደፍረው ለሚነሱት ትብብርን አናሳይም።ጠለቅ አርጐ ለማሰብ ይቸግረናል፣ አንመራመርም፣ አሉባልታ ግን ይቀናናል፣በምንቸገረኝ ሁላችንን የሚጐዳውን በዝምታ ማለፍ እንመርጣለን።ትጋትና ድፍረት አለማሳየት ድክመት ከመሆኑ ጋር የቡድን ተጠቃሚዎች እንደከብት ተከታይ እያደረጉን ነው።

ስለዚህ ነገር ቢያበዙት እውቀት አይሆንም ካላገናዘቡትና ወደ መደምደሚየ ልቃረብና በዚህ በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ያጋጠመውን ከላይ እንደተገለጸው ልብ እያላችሁ በየትኛውም አገርና የአሜሪካ ከተማዎች የምትኖሩ ኢትዮጵያኖች ሁሉ እንደዚህ አይነት ክስተት፤ የባንዳ ባህሪ፣ የፖለቲካ መጠቀሚያ የሚያደርጉ፣ወዳጅ መስለው በአገር ጥቅም ላይ የሚነግዱ በድርጅትና በቡድን ሕገ_ ወጥ እኩይ ተግባርና ባህሪ ያላቸውን ባንዳዎች ሁሉ በቅድሚያ በትጋትና በድፍረት አውቃችሁና ተባብራችሁም እንዲትቋቋሙና ከጥፋት እንድትድኑ የተረዳሁትን ያየሁትንና እየተፈጸመም ያለውን ከብዙ በጥቂቱ ከሞላ ጐደል ትዝብቴን አካፍላለሁ፣ ወደ 15 ደቂቃ በዚህ የገባያ ዝውውር አለቀ። አስገነዝባለሁ።

እግዚአብሔር ፍቅርና ሳላምን ለኢትዮጵያ ይባርክ !